# ETHIOPIAN CIVIL SERVICE UNIVERSITY

# የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ

Quarterly Magazine
April - June 2025



ኢሲሰዩ 2312 ተማሪዎችን በድምቀት አስመረቀ



ECSU Hold the 10th National Research Conference

## ራዕይ

ፐብሊክ ሴክተሩን ከመገንባት አኳያ በ2022 በዘርፉ ከተሰማሩት ተቋማት መካከል የላቀ፣ በቴክኖሎጂ የዘመነና ተወዳዳሪ የአቅም መገንቢያ ተቋም መሆን

## ተልዕኮ

ፐብሊክ ሴክተሩ ውጤታማ የህዝብ አገልጋይ ሆኖ እንዲሰራ አቅሙን በስፔሻላይዝድ ትምህርት፣ በስልጠና፣ በማማከር፣ በጥናትና ምርምር እና በማህበረሰብ አገልግሎቶች በቀጣይነት መገንባት

## እሴቶች

ተገልጋይ ተኮር

ልቆ መገኘት

ተባብሮ መሥራት

ሁሌም መማር

ፈጠራን ማበረታታት

ዘለቄታዊ ውጤታማነት

ብዝሀነትን መቀበል

ትኩረት ልዩ ድጋፍ ለሚሹ

# *Table of contents*


ኢሲሰዩ 2312 ተማሪዎችን በድምቀት አስመረቀ.....1

በኢሲሰዩ ለተመራቂ ተማሪዎች ለሁለት ቀናት ሲሰጥ የቆየውን የኢንዳክሽን ስልጠና ተጠናቀቀ.....3

የኢሲሰዩ ካውንስል የ2017 ዓ/ም የሶስተኛ ሩብ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማና በቀጣይ የሪፎርም ስራዎች አቅጣጫ ላይ ውይይት አደረገ.....4

በኢሲሰዩ በአእምሮ ጤና ጉዳት እና በሱስ አምጪ ልምምዶች ተጋላጭነት ላይ ያተኮረ ስልጠና ተሰጠ.....6

በኢሲሰዩ ሱስ አምጪ ንጥረ ነገሮችን አላግባብ መጠቀምን ለመከላከል ያለመ ስልጠና ተሰጠ.....7

የኢሲሰዩ ማህበረሰብ በህጻናት ማቆያ ረቂቅ መመሪያ ላይ ውይይት አደረገ.....8

በኢሲሰዩ የተካሄደዉ የ12ኛ ክፍል ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተና በስኬት እንዲጠናቀቅ ላደረጉ አካላት የምስጋና መርሃ ግብር ተካሄደ.....8

በኢሲሰዩ የተካሄደዉ የ12ኛ ክፍል ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተና በስኬት እንዲጠናቀቅ ላደረጉ አካላት የምስጋና መርሃ ግብር ተካሄደ.....9

*ECSU Hold the 10th National Research Conference.....10*


*ECSU Holds a Conference on The Right of Landlocked States in Relation to access to Sea under International Law.....12*

# ኢሲሰዩ 2312 ተማሪዎችን በድምቀት አስመረቀ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ (ኢሲሰዩ) በተለያዩ የትምህርት ፕሮግራሞች ያሰለጠናቸውን 2312 ተማሪዎች በመጀመሪያ፣ ሁለተኛና በፒኤች ዲ በአደዋ ድል መታሰቢያ ፓን አፍሪካ የመሰብሰቢየ አዳራሽ ሰኔ 14 ቀን 2017 ዓ.ም በድምቀት አስመረቀ። ከመደበኛ ፕሮግራሙ ባሻገርም ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር ባለው ትብብር በልዩ ፕሮግራም ሲያሰለጥናቸው የቆዩ 24 ዕጩ ዲፕሎማቶችንም በከፍተና ዲፕሎማ ሰርቲፊኬት አስመርቋል።



በምረቃ ስነ ሥርዓቱ ላይ ላይ በክብር እንግድነት የተገኙት ፕ/ር ብርሃኑ ነጋ የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ባስተላለፉት መልዕክት በሀገራችን የተለያዩ የሪፎርም ስራዎች እየተተገበሩና ውጤት እያስገኙ መሆኑን ገልጸው፤ ነገር ግን ሲንከባለሉ በቆዩና ከቅርብ ጊዜያት በኋላ በተነሱ አንዳንድ ክስተቶች ጋር ተያይዞ አጠቃላይ የሆነ የሞራል መናጋት ጋር ተያይዞ ፈርጀ ብዙ ችግሮች እየተፈታተነን እንገኛለን ብለዋል። በሪፎርምም እነዚህን ችግሮች በመፍታት፣ ብሎም አለም አቀፍ ችግሮችንም መቋቋም የሚችል መጪ ትውልድ ማዘጋጀት፣ በብቃትና በአንድነት መስራት የሚገባን ወቅት ላይ እንገኛለን ብለዋል። ትምህርት እነዚህን ችግሮች በመቅረፍ ላይ የማይተካ ሚና የሚጫወት ቢሆንም የትምህርት ዘርፉ በትምህርት ጥራት እና ተያያዥ ጉዳዮች ያጋጠሙት ስባራቶችን የትምህርት ሪፎርም ተቀርጾ በመተግበር ላይ መሆናቸውን እንዲሁም የዩኒቨርሲቲዎች አካዳሚያዊና አስተዳደራዊ ነጻነትም ለማስገኘትም የራስገዝ ዩኒቨርሲቲ ለማቋቋም የራስገዝ አዋጅ ጸድቆ ተግባራዊ እየሆነ መሆኑን እና በትምህርት ሚኒስቴርም ፍኖተ ካርታ ተቀርጾ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል። አያይዘውም በሀገራችን ያለውን የሲቪል ሰርቪስ አገልግሎት የሚታየውን ችግር ለመቅረፍ ከተቋቋሙት ተቋማት መካከል አንዱ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ መሆኑን አስታውሰው ዩኒቨርሲቲው ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ በርካታ ሲቪል ሰርቫንቶችን ማፍራቱን የገለጹት ክቡር ሚኒስትሩ ዩኒቨርሲቲው የተጣለበትን የፐብሊክ ሰክተሩን አቅም የመገንባትና የማዘመን ተልዕኮ ለመወጣት እንዲያስችለው ዩኒቨርሲቲውን በአዲስ መልክ ሪፎርም በማድረግ ሀገራዊ የልዕቀት ማዕከል ለማድረግና በአለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሲቪል ሰርቪስ የሰው ኃይል መገንባት የሚችል ተቋም እንዲሆን በመንግስት መወሰኑን ገልጸው ከትምህርት ሚኒስቴር ፣ ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንና ከዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ ባለሙያዎች የተዉጣጣ የጋራ ግብረ ኃይል ተቋቁሞ ዩኒቨርሲቲው እንደገና በአዲስ መልክ የማጠናከር ጥናት በመጠናቀቅ ላይ መሆኑን ገልጸዋል። በዚህም ለሀገርና ለህዝብ ታማኝ የሆኑ ባለሙያዎች በልዩ ሁኔታ የሚፈሩበት ተቋም ይሆናል ተብሎ እንሚታመንም ገልጸው፤ በሚደረገው ሪፎርም የዩኒቨርሲቲው አመራሮች ፣ሰራተኞችና ባለድርሻ አካላት በቁርጠኝነት እንዲተጉ አሳስበዋል። ተመራቂ ተማሪዎችም ወደየተቋማቸው ሲመለሱ ከአድልዎና ከወገንተኝነት የጸዳ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጡ በአጽንኦት አሳስበዋል። የኢሲሰዩ ፕሬዚደንት ዶ/ር ንጉሥ ታደሰ በበኩላቸው ባደረጉት የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት ለተመራቂዎቹ በብዙ ድካምና ጥረት ያገኛችሁት ውጤት በመሆኑ እንኳን ደስ አላችሁ ብለዋል። ዶ/ር ንጉሥ በማስከተልም የሀገራችን የፐበሊክ ሰርቪስ መንግስትና ዜጎች በሚጠብቁት ልክ ነጻና ገለልተኛ ፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ፈጣን አገልግሎት ለዜጎች ተደራሽ ለማድረግ የሲቪል ሰርቪስ አስተዳደርና አገልግሎት አሰጣጥ ሪፎርም ተቀርጾ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል። የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲም ከምንግዜውም በበለጠ ከኢፌዴሪ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጋር በቅርበትና




በቅንጅት የፐብሊክ ሰርቪሱን አቅም የመገንባት ጉዞውን አጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን አረጋግጠዋል። ዩኒቨርሲቲው ከ34 ሺህ በላይ ምሩቃንን በዲፕሎማ፣



በመጀመሪያዲግሪ፣በማስተርስና በፒኤች ዲ ዲግሪ ማፍራት የቻለ እና 448ምሩቃንን ከተለያዩ ጎረቤት ሀገራ የመጡ የየፐብሊክ ሴክተር ተቋማት ሲቪል ሰርቫንቶችን በማስመረቅ ሀገራችን ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያላትን መልካም ጉርብትናና የውጭ ጉዳይ መርህ በትምህርት መስክ እንዲጠናከር አስተዋጽኦ ማድረግ መቻሉን የጠቆሙት ዶ/ር ንጉሥ ከ200 ሺ በላይ ለሚሆኑ ሲቪል ሰርቫንቶችና አመራሮችም ብቃት ተwኮር ስልጠና በመስጠት ብቃታቸውን ለማሳደግ መቻሉን ገልጸዋል።በጥናትና ምርምር መስክም ከ500 በላይ ሳይንሳዊ የምርምር ፕሮጀክቶችን በማካሄድ በምርምር የተደረሰባቸውን ግኝቶችና አሰራሮች ለሚመለከታቸው የህዝብ አገልግሎት ተቋማት በማሰራጨት ለፖሊሲ ግብአት እንዲሆኑ መደረጉንም ተናግረዋል። ዩኒቨርሲቲው ከመንግስት በተሰጠው ተልዕኮ መሰረት ከታዳጊ ክልሎች ውስጥ የሚገኙ የፐብሊክ ሴክተር ተቋማት እንዲጠናከሩ በልዩ ሁኔታ ፕሮግርም ቀርጾ የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች ያካሄደ እና ውጤት የስመዘገበ መሆኑንና ከተለያዩ ተቋማትም ጋርም በትምህርትና በስልጠና ፣የምርምርና ማማከርስራዎችተከታታይና ቀጣይነት ያለው አቅም በመገንባት ረገድ ውጤት መገኘቱንም ገልጸዋል። ዶ/ር ንጉስ አያይዘውም ዩኒቨርሲቲውየተጣለበትን ኃላፊነት በብቃት ለመውጣት እንዲችል ተቋማዊ፣ አካዳሚያዊና አስተዳደራዊ ነጻነት አስፈላጊ በመሆኑ ራስ-ገዝ ዩኒቨርሲቲ የመሆን ዕቅድን መሰረት በማድረግ የሽግግር ስራዎች እየተሰሩ መሆናቸውንና በዩኒቨርሲቲው የውስጥ ገቢውን ለማሳደግ ጠንካራ የፋይናንስ አቅም ለመፍጠር፣ ብቁና በቂ የሰው ኃይል በማደራጀትና ስትራቴጂያዊ የሰው ኃይል አመራርን ለማጠናከር፣ተመራጭና ተወዳደሪ የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞችን ለማልማት፣ አስቻይ የምርምርና ማማከር ስርዓት ለመዘርጋት፣ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው ልማታዊ ፕሮጀክቶች ላይ ያለውን አበርክቶ ለማጠናከር፣ ደረጃቸውን የጠበቁ የመሰረተ ልማትና ፋሲሊቲዎች ለማደራጀት እንዲሁም የዩኒቨርሲቲውን የመማር ማስተማርና የአገልግሎት አሰጣጥ በዲጂታል ቴክኖሎጂ ስርዓት ለማጠናከር በርካታ ቁልፍ ተግባራትን ቀርጾ ተግባራዊ እያደረገ መሆኑና በ2018 ዓ.ም



ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን የጠበቀ የትምህርትና የስልጠና የልህቀት ማዕከል ለመሆን አልሞ ቁልፍ ተግባራትን በመለየት እየሰራ መሆኑን ገልጸው ፤ አለም አቀፍ ደረጃዎችን የጠበቀ የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች መቅረጽና ተግባራዊ ማድረግ፣ የመማሪያና የስልጠና ክፍሎችን ማዘመን፣ የተጀመሩ ፋሲሊቲዎችን ማጠናቀቅና ወደተግባር እንዲገቡ ማድረግ፣ከሀገር ውስጥና አለማቀፍ መሰል ተቋማት ጋር ያለን ነባርትስስሮችን ማጠናከርና አዳዲስ ትስስሮችን የመፍጠር ስራዎች እንዲሁም ሌሎች ስራዎችም የሚከናወኑ መሆናቸውን እና ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንና ከሌሎች አጋርና ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት በአዲስ መልክ የመቃኘትና ትብብሮችን የማጠናከር ስራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ የሚደረግ መሆኑን በአጽንኦት ተናግረዋል።



# በኢ.ሲ.ሰ.ዩ ለተመራቂ ተማሪዎች ለሁለት ቀናት ሲሰጥ የቆየውን የኢንዳክሽን ስልጠና ተጠናቀቀ።

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የከተማ ልማት እና ምህንድስና ኮሌጅ ከከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በፒኤችዲ እና በማስተርስ ፕሮግራም ትምህርታቸውን ተከታትለው ላጠናቀቁ ተመራቂ ተማሪዎች ሲሰጥ የቆየውን የሁለት ቀናት የኢንዳክሽን ስልጠና አጠናቀቀ። ሰኔ 9 እና 10 /2017 ዓ/ም በተሰጠው ስልጠና ላይ ቁጥራቸው 316 የሆነ ተመራቂ ተማሪዎች ተሳትፈዋል።



በስልጠናው የመዝጊያ መርሀ-ግብር ላይ የተገኙት የከተማ እና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ወ/ሮ ጫልቱ ሳኒ ባደረጉት የእንኳን ደስ አላችሁ ንግግር፣ ተማሪዎቹ ትምህርታቸውን አጠናቀው ለምረቃ በመዘጋጀታቸው የተሰማቸውን ደስታ ገልጸው፣ “ከስልጠናው ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለው ባለው ተጨባጭ ሁኔታ የሀገራችን የከተማ ልማት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ቀድሞ ከነበረው ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ጋር ሲነጻጸር ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ ለውጥ የተደረገበት በመሆኑ፣ ስልጠናው ወደ ስራ ስትሰማሩ ከፖሊሲ እና ከእስትራቴጂ አኳያ ሊፈጠር የሚችለውን የግንዛቤ ክፍተት ለመሙላት የሚረዳ ስልጠና ነው።” በማለት የስልጠናውን ጠቀሜታ



ገልጸዋል። እዚህ ካገኛችሁት እዉቀት በተጨማሪ የራሳችሁን ፈጠራ በማከል በተሰማራችሁበት ሁሉ ለዉጥ እንድታመጡ ፤ለሚቀጥለዉ ትዉልድ መሰረት ጥላችሁ እንድትሄዱ አደራ እያልኩ መልካም የስራ ግዜ እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ ብለዋ።

የኢትዮጲያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ንጉስ ታደሰ ለእጩ ምሩቃን የእንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል። በማስከተልም እንዲህ አይነት ስልጠና ትልቅ ክፍተት እንደሚሞላ በመግለጽ የኒቨርሲቲዉ ከከተማ መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ለእጩ ምሩቃን ስራ ከመጀመራቸዉ በፊት ከፖሊሲዎች ፣ስትራቴጅዎች ፣አዳዲስ የከተማ ልማት ዘርፍ ክንዉኖች እንዲተዋወቁ ማድረጉ በስራ ስምሪታቸዉ ወቅት የሚያጋጥማቸሁን ችግር ይቀርፋል ብለዋል። በስልጠናው ይዘት ውስጥ የተካተቱት፣ ትራንስፎርሜሽናል ሊደርሽፕ፣ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ፖሊሲ፣ የሌጋሲ ከንቲባ አመራር፣ የስማርት ሲቲ ስተራቴጂ፣ የከተማ ልማት ፖሊሲ፣ የከተማ መሬትና መሬት ነክ ምዝገባ አዋጅ፣ የዓላማ መር ፕሮጅክት ቀረፃ፣ እና ሪል እስቴት



ፕሮክላሜሽን የሚሉት ርዕሶች ሲሆኑ ስልጠናውን የሰጡት ከከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር የመጡ፣ በከተማ ልማት ዘርፍ የተሰማሩ ከፍተኛ ባለሙያዎች ናቸው። በስልጠናው መክፈቻ ላይም የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ዘርፍ ም/ፕሬዚደንት ዶ/ር ለማ ጉዲሳ ባደረጉት የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር “እናንተ እዚህ በትምህርት ላይ በቆያችሁባቸው አመታት በሀገራችን በርካታ የከተማ ልማት ፖሊሲ እና ስታራቴጂ ለውጦች ተደርገዋል፤ ይህ ስልጠና ከእነዚህ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር እራሳችሁን እንድታስተዋውቁ ይረዳችኋል።” ብለዋል።



# የኢሲሰዩ ካውንስል የ2017 ዓ/ም የሶስተኛ ሩብ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማና በቀጣይ የሪፎርም ስራዎች አቅጣጫ ላይ ውይይት አደረገ፡፡

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ (ኢሲሰዩ) ካውንስል ሚያዝያ 7 ቀን 2017 ዓ.ም በህዳሴ አዳራሽ ባካሄደው ሶስተኛ መደበኛ የካዉንስል ስብሰባ የ2017 በጀት ዓመት የሶስተኛው ሩብ ዓመት የመደበኛና የሪፎርም ሥራዎች አፈጻጸም ግምገማ እና በቀጣይ የሚተገበሩ የሪፎርም አቅጣጫዎች ላይ ውይይት አካሄደ፡፡



የውይይት መድረኩን በእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር የከፈቱትየኢሲሰዩፕሬዚደንትዶ/ርንጉሥታደሰእንደተናገሩት በዚህ የሶስተኛ ሩብ ዓመት ግምገማ በዋናነት የሩብ ዓመት የመደበኛና የሪፎርም ሥራዎች ሪፖርት መገምገም እና በቀጣይዩኒቨርስቲዉሊያሻግርየሚችል'ግሎባልሰታንድርድ' ያለዉ ተቋም የማድረግ ሂደት ዉስጥ በሚኖረው የሪፎርም አፈጻጸም ፍኖተ ካርታ ላይ አቅጣጫ ማስቀመጥ እና መወያየት ፤ የጋራ ግንዛቤ መያዝ እና ለትገበራዉ ዝግጁ መሆን የሚሉት መሆናቸውን ገልጸዋል፡ ፡በሚቀጥሉት ጊዚያት በዋናነት ተቋሙ በሚሰጣቸዉ የትምህርት፣የምርምር እና የስልጠና ፕሮግራሞችን ማዘመንና ብሎም ወቅቱ ከሚጠይቀው ነባራዊ ሁኔታ መሄድ አማራጭ የሌለው ጉዳይ በመሆኑ በሚፈለገዉ ቁመና ላይ ለመገኘት የሚያስችሉ የሪፎርም ስራዎችን መተግበር አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ለዚህ ትግበራ ሁሉም የዩኒቨርሲቲዉ ማህበረሰብ አሻራዉን ማሳረፍ እንዳለበት አሳስበዋል፡፡ በማስከተልም የሶስተኛው ሩበ ዓመት የመደበኛና የሪፎርም ሥራዎች አፈጻጸም ሪፖርትበስትራቴጂክጉዳዮችሥራአስፈጻሚ በሆኑት በአቶ ተፈሪ ጊሼ የቀረበ ሲሆን በሪፖርታቸው የዩኒቨርሲቲውን ስትራቴጂክ ግቦች ለማሳካት የተሰሩ ዝርዝር ተግባራትና ተቋሙ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር የተፈራረማቸውን ቁልፍ የውጤት አመላካቾች አተገባበር ላይ የተሰሩ ስራዎችን በዝርዝር ተግባራት አመላክተዋል፤ በትግበራዊ ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች እና ለወደፊት ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮችንም ጠቁመዋል፡፡ በቀረበው ሪፖርት መሰረት ከካዉንስል አባላት ለተነሱ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች የየዘርፍ አመራሮች ምላሽ እና ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ በቀጣይም የኢሲሰዩ ፕሬዚደንት ዶ/ር ንጉሥ በተነሱ ሀሳቦች



እና ጥያቄዎች ዘርዘር ያለ ማብራርያእና ምላሽ ሰጥተዋል፡ ፡የዩኒቨርሲቲውን ልዩታ በተመለከተ ለተነሱ ጥያቄዎች የተቋቋመዉ ኮሚቴ በሚያቀርበዉ ሀሳብ መሰረት የሚወሰን መሆኑን አስገንዝበዋል። አያይዘውም ተቋሙን ዘመናዊ እና አለምዓቀፍ ስታንዳርድ ያለዉ የስልጠና ተቋም፣ የተመረጡ የአካዳሚክ ፕሮግራሞችን የያዘ፣ ከፍ ያለ ብቃት ያለው



አመራር እና ተመራጭ ባለሙያዎችን የምናፈራበት ተቋም ፣ ብሎም ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚወክል ተቋም ማድረግ ዋንኛ ትኩረት ተሰጥቶት እንደሚሰራ ገልጸዋል። ለዚህ በመጨረሻም በዕለቱ የቀረበው ሪፖርት በካውንስሉ በማጽደቅ ቀጣይ አቅጣጫ በማስቀመጥ ሶስተኛዉ የካዉንስሉ መደበኛ ስብሰባ ተጠናቋል።

ትግበራ ዩኒቨርሲቲው በቀጣይ ማስቀደም የሚገባው በርካታ ተግባራት መኖራቸውን ገልጸዉ ለዚህም መሳካት ከዩኒቨርስዉ ማህበረስብ ቁርጠኝነት አስፈላጊ መሆኑን አሳስበዋ። ይህንን መነሻ በማድረግ በቀጣይ መሰራት ስላለባቸው ስራዎች አቅጣጫ የሰጡት ዶ/ር ንጉስ በጥልቀት መነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዩኒቨርሲቲው በቀጣይ እንቅስቃሴው ማስቀደም የሚገባው በርካታ ተግባራት መኖራቸውን በመግለጽ አራት አጀንዳዎች ላይ ግን የበለጠ ትኩረት በማድረግመስራትእንደሚያስፈልግበአጽንኦትአሳስበዋል። ከእነዚህ አጀንዳዎች መካከልም የመጀመሪያው በዩኒቨርሲቲው አጠቃላይ ሪፎርም በማድረግ እና ተቋሙን እንደገና በማዋቀር፣ የመማር ማስተማር፣ የምርምር፣ የስልጠና የማማከር እንዲሁም የአስተዳደር ስራዎችን እንደገና በመፈተሸ፤ ሁሉን አቀፍ የሆነ ተቋሙን የማደስ ስራ መስራት መሆኑን አብራርተው ተቋሙን እንደገና የማዋቀሩ ስራ ከተልዕኮ እና ከትኩረት አንጻር የሚሰራ መሆኑን ገልጸዋል። በሁለተኛ ደረጃ የቀረበውም በዩኒቨርሲቲው የተጀመሩት ሁሉንም ስራዎች በታቀዱት መሰረት በተገቢው ሁኔታ ማጠናቀቅ ፣ ሶስተኛው ተግባርም ዩኒቨርሲቲው የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በብሄራዊ ደረጃ እያካሄደ ላለው የሪፎርም ስራ የሚጠበቅበትን በመለየት በባለቤትነት መንፈስ በጋራ የመስራት ጉዳይ መሆኑን ገልጸዋል፤ በአራተኛ ደረጃ የተቀመጠው ደግሞ በተቋሙ የሚታዩ አንዳንድ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመቅረፍ ሁሉም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ለተልዕኮው ስኬት ከልብ እንዲሰራ ማስቻል መሆኑን ገልጸዋል።



# በኢሲሰዩ በአእምሮ ጤና ጉዳት እና በሱስ አምጪ ልምምዶች ተጋላጭነት ላይ ያተኮረ ስልጠና ተሰጠ።

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ሚያዝያ 1 እና 3 ቀን 2017 ዓ/ም በአካባቢው ለሚገኙ የአእምሮ ጤና ጉድለት እና ለሱስ አምጭ ልምምዶች ተጋላጭ ለሆኑ 36 ወጣቶች እና የማህበረሰብ ክፍሎች የሁለት ቀን ስልጠና ሰጠ።



ስልጠናው በዩኒቨርሲቲው የምርምርና ትብብር ዘርፍ በ2017 ዓ/ም ታቅደው እየተከናወኑ ካሉ ተግባራት መካከል አንዱ መሆኑን የማህበረሰብ አሳታፊነትና ኢንዱስተሪ ትስስር ቴክኖሎጂሽግግርዳይሬክቶሬትዳይሬክተርከሆኑትዶ/ርዮናስ አበሻ ገለጻ ለመረዳት ተችሏል።



በስልጠናው ሱስ አምጪ ንጥረ ነገሮችን አላግባብ መጠቀም ፣ በጤና እና በማህበራዊ ህይወት ላይ የሚያስከትለውን ቀውስ እና አሉታዊ ውጤቶችን ለመከላከል የሚያስችል ግንዛቤን ለማስጨበጥ ያለመ ነው ተብሏል። ሰልጣኞቹም ከስልጠናው በኋላ በሰጡት አስተያየት፣ ከስልጠናው በርካታ ቁም ነገር መገብየታቸውን ገልጸው፣ "ስልጠናው ትውልድን ብሎም ሀገርን የማዳን ጉዞ መጀመሪያ ነው ብለዋል።" እስከትለውም፣ "መርሃ ግብሩ ከዚህ ሰፋ ያለ ተደራሽነት ቢኖረው መልካም ነው።"፣ "ይህንን ለሚያህል አገራዊ ቁም ነገር የሁለት ቀን ስልጠና በቂ አይደለም።"፣ "በስልጠናው ላይ ለተነሳው ችግር ተግባራዊ የሆነ የመፍትሄ አቅጣጫ ቢቀመጥለት ጥሩ ነው።"፣ "በዩኒቨርሲቲው ለማገገሚያ የሚሆን የማማከሪያ ማዕከል ቢቋቋም ጥሩ ነው።" የሚሉ አስተያየቶችን ሰጥተዋል።

በስልጠናው ማጠናቀቂያ ላይ የዩኒቨርሲቲው የማህበረሰብ አሳታፊነት፣ ኢንዱስተሪ ትስስር እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ዶ/ር ዮናስ አበሻ ከሰልጣኞች ለተነሱ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች ምላሽ የሰጡ ሲሆን፣ አንዳንዶቹ ጥያቄዎች የአስተዳደር አመራርን ምላሽ የሚጠይቁ በመሆናቸው ለበላይ ኃላፊዎች እንደሚያቀርቡ፣ በዳይሬክቶሬቱ አቅም የሚመለሱ ጉዳዮችን ለማስተናገድ ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል፡ ፡ ስልጠናውን የሰጡት በዘርፉ ከፍተኛ ልምድ ያላቸው የዩኒቨርሲቲው የሶሻል ፖሊሲ ጥናት መምህራን ናቸው።

በቀጣይም በሱስ አምጪ ንጥረ ነገሮች ላይ ተመሳሳይ ግንዛቤ ለመፍጠር የሚያስችል ስልጠና በአካባቢው ለሚገኙ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች፣ ህገ-ወጥ ስደት እና የማህበረሰብ ተሳትፎ በሚሉ ዋና ዋና ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ስልጠና የችግሩ ኢላማ ለሆኑ ታዳጊ ወጣቶች እና ለባለድርሻ አካላት ለመስጠት ዝግጅቱ የተጠናቀቀ መሆኑን ከተያዘው መርሃ ግብር ለመረዳት ችለናል። ዩኒቨርሲቲው መጋቢት 6 ቀን 2017 ዓ/ም ጀምሮ ለ2ኛ ደረጃ መምህራን እና ተማሪዎች የተለያዩ ስልጠናዎችን እና በሳይንስ የትምህርት ዘርፎች ቲቶሪያል ሲሰጥ መቆየቱ ይታወሳል።

# በኢሲሰዩ ሱስ አምጪ ንጥረ ነገሮችን አላግባብ መጠቀምን ለመከላከል ያለመ ስልጠና ተሰጠ፡፡

የኢትዮጵያሲቪልሰርቪስዩኒቨርሲቲ(ኢሲሰዩ)በአካባቢዉከሚገኙሁለተኛደረጃትምህርትቤቶችለተውጣጡ35ተማሪዎች፣ የአእምሮ ጤና እና ሱስ አምጪ ንጥረ ነገሮችን አላግባብ መጠቀምን መከላከል (Mental Health and Prevention of Sub-stanceAbuse)በሚልርዕሰጉዳይላይከሚያዝያ17እስከ18ቀን2017ዓ.ምየሁለትቀናትየግንዛቤማስጨበጫስልጠናሰጠ፡፡



ስልጠናው ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የተሰጠበት ምክንያት፣ የነገ ሀገር ተረካቢ ተማሪዎች እንደመሆናቸው መጠን፣ ሱስ አምጪ የሆኑ አደገኛ ንጥረ ነገሮችን አላግባብ መጠቀም በሚያስከትለው የትውልድ ክፍተት ላይ በቂ እውቀት ኖሯቸው እራሳቸውን እና ማህበረሰቡን እንዴት መከላከል እንዳለባቸው ለማስገንዘብ መሆኑ ከስልጠናው ሂደት ለመረዳት ተችሏል፡፡ ስልጠናውን የሰጡት በዘርፉ የካበተ



እውቀት እና ልምድ ያላቸው የዩኒቨርሲቱው መምህራን ናቸው፡፡ በማጠቃለያው ላይ በስልጠናው የተሳተፉት ተማሪዎች ከተሰጣቸው ስልጠና በርካታ ጠቃሚ ቁም ነገሮች ያገኙ መሆናቸዉን የገለጹ ሲሆን ስልጠናው ካለው ስፋት አንጻር ሁለት ቀን እንደሚያንሰው እና በመደበኛ የትምህርት ወቅት ከሚሰጥ ይልቅ በክረምት ወይም በዝግ ወቅት ቢሰጥ በቂ ጊዜ ወስዶ ተገቢውን ግንዛቤ ማስጨበጥ ያስችል እንደነበረ እና ሌሎችንም ገንቢ አስተያየቶች ሰጥተዋል፡፡



ስልጠናውን ያዘጋጀው በዩኒቨርሲቲው የምርምርና ትብብር ዘርፍ የማህበረሰብ አሳታፊነትና ኢንዱስተሪ ትስስር ቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬት ሲሆን በተመሳሳይ ከመጋቢት 6 ቀን 2017 ዓ/ም ጀምሮ በአካባቢው የሚታዩ ችግሮችን እና ለማህበረሰቡ ስጋት የሆኑ ጉዳዮችን በጥናት በመለየት፣ ለተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ልዩ ልዩ ስልጠናዎችን እየሰጠ መሆኑን የዳይሬክቶሬቱ ሃላፊ ዶ/ር ዮናስ አበሻ ገልጸዋል፡፡

## የኢሲሰዩ ማህበረሰብ በህጻናት ማቆያ ረቂቅ መመሪያ ላይ ውይይት አደረገ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ (ኢሲሰዩ) ማህበረሰብ በቅርቡ ሥራ ለሚጀምረው የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የህጻናት ማቆያ የሚመራበት ረቂቅ መመሪያ ላይ ውይይት አደረገ።

በውይይት መድረኩ ላይ በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች አካትቶ ትግበራ ሥራ አስፈጻሚ በኩል የተዘጋጀው ረቂቅ መመሪያ የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች ልጆቻቸውን ወደ ማቆያው በሚያመጡበት ወቅት ሊከተሏቸው የሚገቡ ህጎችን እና ሊያሟላቸው የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች በዝርዝር የቀረበ ሲሆን የውይይቱ ተሳታፊዎችም በቀረበው ረቂቅ መመሪያ ላይ ያላቸውን ሃሳብና አስተያየት አቅርበዋል፡ ፡ መስተካከል ይገባቸዋል ያሏቸውን ሀሳቦችንም የጠቆሙ ሲሆን የህጻናት ማቆያውም በአግባቡ ተደራጅቶ በፍጥነት ሥራ እንዲጀምር እንዲደረግ ጥሪአቸውን አቅርበዋል። ለቀረቡት አስተያየቶችና ጥያቄዎችም ምላሽ እና መብራሪያ የሰጡት የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች አካትቶ ትግበራ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ዝናቤ ታደሰ ተሳታፊዎች ለሰጧቸው ለመመሪያ መዳበር ግብዐት የሚሆኑ ሀሳብና አስተያቶች አመስግነውና የህጻናት ማቆያውን የማደራጀት ሂደት በተሟላ መልኩ በመጠናቀቅ ላይ መሆኑን ጠቅሰዋል።የፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ሃላፊ ዶ/ር አብረሃም ሐጎስ የህጻናት ማቆያዉ በቅርቡ ሥራ እንደሚጀምር በመግለጽ የቀረቡት ማዳበሪያ ሀሳቦች ተካቶ መመሪያዉ የሚጸድቅ መሆኑን ገልጸዋል።



## በኢሲሰዩ የተካሄደዉ የ12ኛ ክፍል ትምህርት ማጠናቀቂያ ፈተና በስኬት እንዲጠናቀቅ ላደረጉ አካላት የምስጋና መርሃ ግብር ተካሄደ።

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ በተካሄደዉ የ2017 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል የተፈጥሮ ሳይንስ እና ማህበራዊ ሳይንስ በወረቀት እና በበይነመረብ ሲሰጥ የነበረዉ ፈተና በስኬት እንዲጠናቀቅ ላደረጉ ተቋማትና አስፈጻሚ አካላት የምስጋና ፕሮግራም ተካሄደ ።

የኢትዮጵ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ንጉሡ ታደሰ (ዶ/ር) በዩኒቨርሲቲው በሁለት ዙር ሲሰጥ የቆየው ሀገር አቀፍ የ12ኛክፍልማጠናቀቂያፈተናበስኬትመጠናቀቁንአስመልክቶ በተዘጋጀው የምስጋና ፕሮግራም ላይ ባደረጉት ንግግር "ፈተናው ፍጹም ሰላማዊ በሆነ ሂደት ተጠናቋል።"ብለዋል። ፕሬዚዳንቱም ከፈተናው ቅድመ ዝግጅት ጀምሮ ፈተናው በስኬት እንዲጠናቀቅ ከፍተኛ ስራ ሲሰሩ ለነበሩ አካላት እና ኃላፊነታቸዉን ለተወጡ የዩንቨርሲቲዉ ከፍተኛ አመራሮች ፤ የፈተና አስፈፃሚ ግብረ-ኃይል አባላት፣ የጣቢያ ኃላፊዎች፣ ሱፐርቫይዘሮች፣ ፈታኞች፣ የፀጥታ አካላት፣ለአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ እና ለኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ተወካዮች ፤ ለትምህርት ሚኒስትር ተወካዮች እና ለሌሎች አገልግሎት ሰጪ አካላት ላከናወኑት ዉጤታማ ተግባር ምስጋና አቅርበዋል። በመጨረሻም በሁለቱም ዙር የተሰጠው ፈተና በስኬት እንዲጠናቀቅ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረጉ የትምህርት ፅህፈት ቤቶች እና አመራሮች፣ ለጸጥታ ክፍሎች እና አመራሮች እንዲሁም ለግብረ ኃይል አባላት የምስክር ወረቀት ሰጥተዋል።







# በኢሲሰዩ ሲሰጥ የቆየው የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ መልቀቂያ ፈተና በስኬት ተጠናቀቀ ፡፡

በኢትዮጵያሲቪልሰርቪስዩኒቨርሲቲ ከሰኔ232017ዓ.ምእስከከሐምሌ8ቀን2017ዓ.ምድረስበበይነመረብእናበወረቀትሲሰጥ የቆየው የ2017ዓ.ም የ12ኛ ክፍልሀገርአቀፍመልቀቂያፈተና ያለምንምእንከንሙሉበሙሉሠላማዊበሆነመንገድተጠናቋል።



የኢሲሰዩ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ንጉሥ ታደሰ ባስተላለፉት መልዕክት በዩኒቨርሲቲው ሲሰጥ የቆየው የ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና በተሳካ ሁኔታ ተጀምሮ በሰላም የተጠናቀቀ መሆኑን በመጥቀስ ፤ፈተናዉ ፍፁም ሰላማዊና ስኬታማ በሆነ መልኩ እንዲጠናቀቅ የየራሳቸዉን ድርሻ እና ሀገራዊ ኃላፊነታችሁን ለተወጡ የዩንቨርሲቲዉ ከፍተኛ አመራሮች ፤ የፈተና አስፈፃሚ ግብረ-ኃይል አባላት፣ የጣቢያ ኃላፊዎች፣ ሱፐርቫይዘሮች፣ ፈታኞች፣ የፀጥታ አካላት፣ በተመሳሳይ ለሌሎች አገልግሎት ሰጪ አካላት ምስጋና አቅረበዋል።












# *ECSU Hold the 10th National Research Conference*

Ethiopian Civil Service University (ECSU) Research Affairs Directorate (RAD) held the 10th National Research Conference on Public Sector Transformation and Development from May 12-13, 2025 at Hidasse Hall. At the conference ESCU scholars, Stakeholders, Researchers and Invited guests from Federal Institutions, Universities, and Addis Ababa City Administration took part.

In his keynote address, Dr. Mekuria Haile, Com-



missioner of the Federal Civil Service Commission, noted that the conference reflects the collective commitment of the Ethiopian Civil Service University and the Federal civil Service Commission to strengthen the public service and governance through research, dialogue and innovation. He added that governance is not a matter of policy and procedures, it is a dynamic process that must adapt to changing societal needs, technological advancements, and emerging global realities. Thematic research in public service and governance is crucial for tackling the pressing challenges within the public service system. These researches need to addresses the increasing demands for transparency, efficiency, responsiveness, empathy, and accountability. To meet these challenges, research must be more than academic and must be actionable, problem solving, transformative and pragmatic. It should go beyond analysis of theories and find solutions for real challenges of the institutions and societies. Hence it is important to identify bottlenecks in service delivery, analyze inefficiencies in institutional operations, explore how digital technologies can enhance accountability and access, and evaluate the impact of governance reforms on citizens' daily lives, Dr. Mekuria underscored. He also emphasized the importance of digital services and governance. With the rapid growth of digital infrastructure, we have the tools to redesign government services for the public. However, the success of digital transformation relies not just on technology but also on human-centered design, institutional readiness, and effective policy frameworks. Research can help this by examining what works, what doesn't, and the reasons behind these outcomes, he noted. The future direction of Ethiopian Civil Service University's academic inquiry should align with practical needs. Good governance is an ongoing journey, and research acts as a guiding compass. ECSU,



with its legacy and potential, plays a vital role in this journey, and encourage the interdisciplinary collaboration between technologists, social scientists, policy makers and civil servants, Dr. Mekuria stressed. Finally, He also requested the presenters and participants of the conference, to think boldly, to change assumptions and to stay grounded in the real problems facing the people and assured them that the knowledge generated doesn't remain on the shelves of the academia but moves to the corridor of the public institutions. In his opening speech, Dr. Nigus Tadesse, ECSU President, on his part, welcomed the participants and said that ECSU and Federal Civil Service Commission are bonded by a shared mission to strengthen and modernize public service. The presence of the commissioner signifies a renewed partnership, emphasizing the commitment to collaboratively ad-

vance their common vision of a free, modern, and effective civil service, Dr. Nigus said. He also mentioned that ECSU continues to work closely with the commission and is dedicated to the implementation of the new Civil Service Reform Policy currently under implementation at selected federal ministries and public sector organizations. He also highlighted the participants of the conference the overall achievements and contributions of the University in the last three decades in building the capacity of the public sector of the country in specialized education programs, need-based short term trainings. In addition, driven by one of the university's mission plan, ECSU has undertaken more than 500 research projects and communicated their finding to public sector institutions, policy makers, including in the form of policy briefs, Dr. Nigus said. ECSU aims to become an African training hub for public service by implementing essential structural and organizational reforms to offer certified training and educational programs for public servants and leaders in Ethiopia, Africa, and beyond, Dr. Nigus underlined.



On the conference a total of 33 research papers which underwent a rigorous review process, were presented. The thematic area distribution of these researches included Economic and development, Urban Governance, Leadership and Development, Diplomacy, International Relations and Cross-cutting issues, HRM, Environment and Development.

Participants on their part, expressed their appreciation for the university and the conference organizers, offering suggestions for future events. Notably, they emphasized the importance of including government officials, practitioners, policymakers, and stakeholders in future to attend the conferences.

Finally, he requested all participants to engage actively in the conference and expressed his gratitude to the organizers of the conference for their efforts in making the conference successful.

In his closing remarks, Dr. Alemayehu Debebe, Vice President for Research and Partnership, sincerely thanked the participants for their participation and expressed his firm hope that the relationships and solidarity established at the conference would continue to further strengthened both individual and institutional levels. He also extended his gratitude to the paper presenters and the organizers for their contributions to the conference's success.



# *ECSU Holds a Conference on The Right of Landlocked States in Relation to access to Sea under International Law*

Ethiopian Civil Service University (ECSU) College of Leadership and Governance, Department of Diplomacy and International Relations and Department of Federalism Studies in collaboration with Austrian Embassy organized a Conference on "The Right of Landlocked States in Relation to access to Sea under International Law," on May 21, 2025.



Lemma Gudissa (PhD), ECSU Vice President for Academic Affairs, welcomed all Honorable guests, Ambassadors, Academic staffs, Invited guests and Students. He also thanked H.E. Ambassador Gregor Schusterschitz for his interest to share his experience on the issues of land locked states for ECSU academia. He also emphasized the overall importance of proximity to the coast, securing a reliable and sovereign path to the sea by examining Ethiopia's rights under international law, exploring the legal principles that govern access to the sea and the solutions available when coastal states avoid such access. Therefore, it is essential to establish a clear understanding of the legal framework that underpins the right of landlocked states to access the sea, he remarked. Speaker of the seminar, H.E. Ambassador Gregor Schusterschitz, outlined legal issues regarding the right of Landlocked States in relation to access to sea under International aw. The United Nations Convention on the Law of the Sea (UNCLOS) that clarifies on the rights of landlocked countries, including participation in the exploitation of coastal states' offshore resources and negotiation of transit transport agreements governing customs, infrastructure, and dispute resolution. By upholding these international law principles and mechanisms, landlocked countries can overcome geographic barriers, benefit from maritime trade, and develop their economies, he mentioned. Under the United Nations Convention on the Law of the Sea, landlocked states are entitled to transit rights through neighboring coastal states to facilitate trade and economic development. Article 125 guarantees the right of access to and from the sea, including the use of ports and transportation infrastructure. Article 127 mandates freedom of transit, prohibiting coastal





states from imposing unnecessary restrictions or excessive tariffs. And also, Article 131 ensures that ships flying the flag of a landlocked state receive equal treatment in transit-state ports. While these provisions offer legal grounds for Ethiopia to assert its rights, the effectiveness of the United Nations Convention on the Law of the Sea in resolving disputes he emphasized He concluded, ensuring access to the sea will require a multidimensional approach—one that blends legal rights with diplomatic pragmatism and strategic alliances. By exploring the legal principles, Ethiopia can work toward a sustainable and enforceable solution that guarantees its rightful place in the global maritime economy. H.E. Ambassador Gregor Schusterschitz, is an Ambassador and legal advisor for the Ministry of European and International Affairs and also Honorary Professor for European and International Law at the University of Innsbruck.

## ግንቦት 14 ቀን 2017 ዓ/ም የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ገላን ጉራ የመኖሪያ መንደር፣ ቡልቡላ ፓርክ እና አዲስ ኢንተርናሽናል ኮንቬንሽን ማዕከልን ጎበኙ።




## ግንቦት 15 ቀን 2017 ዓ/ም "ትውልድ በመምህራን ይቀረፃል፤ ሀገር በትምህርት ይበለጽጋል!" በሚል መሪ ቃል የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ መምህራን የአንድ ቀን የዉይይት መድረክ አካሄዱ።

